# አቶ አሊ ሁሴን የኢፖእአኮ (SOCEPP) ፕሬዚዴንት በኦስሎ፤

የኢትዮጵያ ፖለቲካ እሥረኞች አንድነት ኮሚቴ ፕሬዚዴንት አቶ አሊ ሁሴን ቅዳሜ ኦገስት 31, 2013 ነበር ከለንደን በመለስ ወደ ኦስሎ ጎራ ያሉት። በዚህ ተጋባዥ ሙስሊምና ክርስትያን ኢትዮጵያን በተገኙበት ስብሰባ አቶ አሊ ሁሴን በሰብዓዊ መብት ዙሪያ በተለይ በወቅቱ በወያኔ እየተደርገ ባለው የሰብዓዊ መብት ረገጣ በተለይ በሙስሊም ወንድሞች፣ እህቶችና አረጋውያን ላይ እየተፈጸመ ያለውን የእምነት መብት ጥሰት እንዲያም ሲል ወከባ፣ ጭፍጨፋና ግድያ በማውገዝ ችግሮችንና መፍትሔዎችን የጠቆመ ሰፊ ያለ ማብራሪያና ትንተና በመስጥት በታዳሚው ዘንድ ድብልቅልቅ ያለ ስሜትን የፈጠረ ሳቅና ለቅሶን ያፈራረቀ፣ የእሥርቤት ትውስታዎችን ብሎም የጨካኝ አረመኔዎችን ተግባር ምን ይመስል እንደነበር ያሳየ ታርካዊ ምሥክረንትን የሰጡበት መድረክ ነበር።




ከዚህ ቀደም የኢሕአፓ አመራሮች ደብዛቸው በመጥፋቱ ምክንያት የዛሬ 18 ዓመት የተመሰረተው የኢትዮጵያ ፖለቲካ እሥረኞች አንድነት ኮሚቴ እስካለንበት ጊዜና ሰዓት በስብዓዊ መብት ጥሰት ዙሪያ የማይናቅ አስተዋጽኦ ማበርከቱን ገልጸው በሴቶች እህቶች ክብር ላይ ያተኮረ ግጥም ለቤቱ አቅርበዋል። ከዚያም በመቀጠል ኢትዮጵያ ውስጥ በእርግጥ አክራሪ አሸባሪ አለ ውይ? የሚል ጥያቄ ለታዳሚው ወርውረው ሴቶቻችን አይማሩ፣ ክርስቲያኑን ጨፍጭፉ፤ ሙስሊሙ ሕብረተሰብ በሻሪያ ሕግ የተዳደር ብለዋል??? አላሉም። ታዲያ እስቲ አንድ ምልክት ስጡኝ፡ ሲሉ ቤቱ በዝምታ ድባብ ከመዋጥ በቀር የሰጠው መልስ አልነበረም።

የሙስሊሙ ሕብረተሰብ ጥያቄን አስመልክቶ ያጠነጠነው በሶስት መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ለዚያውም ውኃ የሆኑ በእስላሙ ዘምዘም የምንለው በክርስቲያኑ ደግሞ ፀበል እንደሚባሉት ፈዋሽ የሆኑ ጥያቄዎች ለራሱ ለወያኔ

እንኳን መድኅን የሚሆኑ ጥያቄዎች ናቸው። እኒህ ጥያቄውች ግልጽ የሆኑ ጥያቄዎች እንደመሆናቸው መጠን የቀረቡት፡-

1 ኛ) ሙስሊሙ ያልወከለው አካል በሙስሊሙ ሊተካና ሊመረጥ ይገባል፡ ሙስሊሙን  የማይወክሉት አካሎች ይውረዱልን (መጅሊሳችንን እራሳችን እንምረጥ።)

2 ኛ) በሙስሊሙ ላይ እየተጫነ ያለው አህባሽ የሚለው አስተምህሮት ይቁም፡ ብዚህ ሥር ሙስሊሙን ይህን ተከተሉ የሚለው የመንግሥት የኃይል ጫናና ጣልቃ ገብነት ይቁም።

3 ኛ) አወሊያ የሙስሊሙ ተቋም ስለሆነ መንግሥት ከተቋሙ ላይ እጁን ያንሳ፡ አወሊያን አትንኩብን ነው።

ኢትዮጵያ አገራችን የ 347.000 እሥረኞች ቤት ሆናለች የወያኔ ጥይት እስላም ክርስቲያን አይለይም በዋልድባ የተገደሉ ክርስትያኖች አሉ፡ የወያኔ ውሸት ድንበር የለውም።



ከዛሬ 42 ዓመት በፊት ያነሳነው ጥያቄ እስከዛሬ አልተመለሰም በማለት በለጋ እድሜ መፈክሩን የጻፉበትን እጅ ለታዳሚው በማንሳት አሳይተዋል። በየጣልቅውም ከድንቅዬ ግጥሞቻቸው እማችን ሴት ነች፣ ለምን ይሙት ድሃ፣ ውኃንማ ብሆን፣ ውይት አውቄ ስድብን በቃላቸው በሚያስደንቅ ሁኔታ እንደ ውርድ ነባብ ለቤቱ አቅርበዋል።

አብዛኛው የታዳሚው ጥያቄ ያጠነጠነው በሙስሊሙና ክርስቲያኑ የህብረት ትግል ላይ ነበር፣ ክርስቲያኑ ከሙስሊሙ ጋር በመቅምና በጋራ መታገል አለበት፣ የሙስሊሙ ጥያቄ ላይ ብቻ ከማጠንጠን ለምን ሰፋ አያደርጉትም ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ችግሮች እኒህ ብቻ አይደሉም ወዘተ.የሚሉ ሃሳቦች ሲሰነዘሩ ተደምጠዋል።

አቶ አሊም ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ በመስጠት በተለይ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ጥያቄን ለማዳፈን ከአልቃይዳና አልሻባብ ጋር ለማገናኘት እየተሞከረ ያለው የወያኔ ውሸት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ተቀባይነት አለማግኘቱን ገልጸው እኔ እንደ አንድ ሰብዓዊ መብት ተሟጋች ጠመንጃ አንሱ አልልም የኢትዮጵያ ፖለቲካ እሥረኞች አንድነት ኮሚቴን (SOCEPP)
የሙስሊሙ ሃይማኖት ጠበቃ ብቻ አድርጎ ማየቱ ስህተት ነው እኛ ለሁሉም ነው የምንጮኸው ብለዋል።



በመጨረሻም የኢትዮጵያ ፖለቲካ እሥረኞች አንድነት ኮሚቴ (SOCEPP) ን እርዱ ብለው መልእክታቸውን ለታዳሚው አስተላልፈዋል።



